በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

***ቦታ፦*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሚያዝያ ፱ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# <u>ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ</u>

## <u>ንስሐ</u>

- ንስሐ ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ነው፡፡
- በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሰው ከተሳሳተ ንስሐና ኑዛዜ ያስፈልገዋል፡፡ ***<u>ሉቃ 15፡7-10፡፡</u>***
- ኑዛዜ ኃጢአትን መናገር ብቻ ሳይሆን ኃጡአተኛውን ወደ ንስሐ የሚመራ የጸጸት ስሜትም ጭምር ነው፡፡

***<u>ኑዛዜ</u>***

1. እንደ ልበ አምላክ ዳዊት ለእግዚአብሔር ይቀርባል፡፡ ***<u>መዝ 50፣ መዝ 6፡፡</u>***
2. የእግዚአብሔር ውክልና ላለው ለንስሐ አባት ይቀርባል፡፡ ***<u>ቀዳ ቆሮ 4፡1፣ ሚል 2፡7፣ ማቴ 18፡18፣ ዮሐ 20፡20-23፡፡</u>***
3. የበደልነው ሰው ካለ ለተበደለውም ሰው ስላደረግነው ክፋትና ስለፈጸምነው ጥፋት እንናገራለን፡፡ ***<u>ማቴ 5፡23-24፡፡</u>***
4. ራሳችን በሐሳብ ለሠራነው ኃጢአት በድያለሁ ብለን ራስንም መውቀስ እንደ ኑዛዜ ይቆጠራል፡፡ ኑዛዜ የሚጀምረው ከራስ ነውና እንደ ሰማርያ ሰዎች የራሳችንን ኃጢአትና ድካም ረስተን ሌሎችን ሰዎች ወይም ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን የምንወቅስ ወይም የምንከስ መሆን አይገባንም፡፡

# ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

***ለኑዛዜ የሚቀርብ ሰው ስሜት የሚከተለውን መምሰል ይኖርበታል፡-***

- **ልበ አምላክ ዳዊት** ‹‹በጭንቀቴ ደክሜያለሁ ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ፥ በዕንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ።›› **መዝ 6፡6፡፡ እንዳለ በፊትህ ክፋትን አደረግሁ ብሎ ስለ በደልነው በደል ማፈርና ማዘን፡፡**
- **ልበ አምላክ ዳዊት** ‹‹በሂሶጵ እርጨኝ፥ እነጻማለሁ እጠበኝ፥ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ።›› **መዝ 50፡6፡፡ ማለትና ወደ ኃጢአት የወሰዱንን በሮች ሁሉ መዝጋት፡፡**
- **ኃጢአትን መሥራት ሕገ እግዚአብሔርን መጣስ፣ አለመታመንና ዓለምን መውደድ እንደሆነ ማወቅ፡፡** ‹‹ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም።›› **ቀዳ ዮሐ 2፡15፡፡**
- **ጻድቅ ዮሴፍ እንዲበድል የተመቻቸለትን አጋጣሚ** ‹‹ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?›› **ዘፍጥ 39፡9፡፡ በማለት እንዳልተጠቀመበትና እንዳልተቀበለው ማስተዋል፡፡**
- ‹‹ኢያሱም አካንን፡- ልጄ ሆይ፥ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ፥ ለእርሱም ተናዘዝ ያደረግኸውንም ንገረኝ አትሸሽገኝ አለው።›› **ኢያ 7፡19፡፡ እንዳለው ንስሐ በካህኑ አማካኝነት በእግዚአብሔርና በኛ መካከል ግኑኝነት የሚደረግበት ምስጢር ነው፡፡ የሚጸለየው የንስሐ ጸሎትም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡**
- **ኑዛዜ ክርስቶስ ሸክማችንን እንዲሸከምልን አሳልፈን መስጠት ነው፡፡ ኢሳ 53፡5-6፣ ዘሌዋ 5፡5፡፡ ጌታችን ሸክማችንን እንዲሸከምልን የሚያደርጉት እምነትና ንስሐ ናቸው፡፡ ዮሐ 3፡16፣ሉቃ 13፡3-5፡፡ ከኃጢአታችን ፈጽሞ የሚያነጻንም ቅዱስ ቁርባኑ ነው፡፡ ቀዳ ዮሐ 1፡7፡፡**
- **ልበ አምላክ ዳዊት ኃጢአቱን በመናዘዙ ምክንያት አትሞትም የሚል ቃል ኪዳንን ተቀብሏል፡፡ ካል ሳሙ 12፡13፡፡**

# ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

***ለኑዛዜ ስንቀርብ የሚከተሉትን ልብ እንበል፡፡***

1. ኑዛኤያችንን የሚቀበለውን የንስሐ አባታችንን ጤና፣ ጊዜ፣ ኃላፊነት … ከግምት በማስገባት ፣ ከኛ ቀጥሎ ለመናዘዝ ቀጠሮ ያላቸው እንዳሉ ባለመርሳት ኑዛዜውን የማያስፈልጉ ረጃጅም መግቢያዎችን በመጨመር ወይም ንግግራችን በማስረዘም ጊዜ ከመውሰድ እንቆጠብ፡፡
2. እግዚአብሔር በኑዛዜያችን ያዘጋጀልንን ጥቅም (በረከት) የምንቀበለው በኑዛዜያችን ግልጽ የሆንነውን ያህል እንደሆነ እንወቅ፡፡
3. የንስሐ አባታችን እንድንርቃቸው የነገሩን ሰዎች ወይም ቦታዎች ካሉ ይህን የነገሩንን ምስጢር ጠብቀን ምክራቸውን ተፈጻሚ እናድርግ፡፡
4. አስቀድመን የወሰንበት ጉዳይ ካለ የንስሐ አባታችንን ስምምነት ለማግኘት ከማስረዳትና ከመጠየቅ በቀር ለማሳመን እንደ ማልቀስ ወይም ክርክር የመሰሉ መንገዶችን አንከተል፡፡
5. ማወቅ የሌሉብንን የቤ/ክ ፖሊሲ ወይም ዜናዎች… ጉዳዮች ካላወቅን ብለን የንስሐ አባታችንን ከማስጨነቅ እንቆጠብ፡፡
6. በንስሐ አባታችን እምነት እናሳድርበት እንጂ ማስረጃ ወይም ማረጋገጫ ስንጠይቅ አንገኝ፤ የሚያጠራጥረንም ጉዳይ ቢኖር በቁጣ ሳይሆን በትሕትና እንጠይቅ ወይም እናስረዳ፡፡

# ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

***ለኑዛዜ ስንቀርብ የሚከተሉትን ልብ እንበል፡፡***

7. በንስሐ አባታችን ፊት ስንቆም በእግዚአብሔር መልእክተኛ አባት ፊት እንደቆምን እናስተውል፣ ፍጹምም ታዛዥ፣ አክብሮት የምንሰጥ ታማኞች እንሁን እንጂ እኩያችን አድርገን አንቁጠር፡፡
8. የተለየ ጉዳይ ያላቸውን የሚንከባከብበትን ሁኔታ ተመልክተን ሥጋዊ ቅናት አይደርብን፣ ምክንያቱንም ለማወቅ ግፊት ማድረግ በኑዛዜ ምስጢራዊነት ጣልቃ እንደመግባት ስለሚቆጠር ይህን ከማድረግ እንቆጠብ፡፡
9. ካህኑ ከሌሎች በተለየ ሁኔታ ለምን እንደምትገናኙ ጥያቄ የሚፈጠርባቸው ሰዎች ስለሚኖሩ ወይም ካህኑንም ሊያስቆጣው ስለሚችል በሆነው ባልሆነው ወደ ንስሐ አባታችን አንመላለስ፡፡ የንስሐ አባታችን ሲገስጹንም ቁጣው ለራሳችን ጥቅም እንደሆነ ልብ እንበል እንጂ አንበሳጭ፡፡
10. ጥያቄ ጠይቀን የንስሐ አባታችን በዝምታ አልፈውት እንደሆነ የዝምታው ምንጭ የጥያቄያችን ትክክለኛ አለመሆን ወይም የሚያስከትልብን ጉዳት ሊሆን ስለሚችል ዝምታውን እንደስምምነት ከመቁጠር እንቆጠብ፡፡
11. ስንናዘዝ የድርጊቱን (የታሪኩ) ግማሽ ገጽታ ብቻ ሳይሆን ሙሉውን እንናዘዝ፡፡
12. ለኑዛዜ ስንቀርብ ሙሉ ለሙሉ በራሳችን ኃጢአት ላይ ትኩረት እናድርግ እንጂ አጋጣሚውን ሌሎችን ለመውቀስና/ለመክሰስ ወይም ስለ ስህተታቸው የምንወነጅልበት አድርገን አንጠቀምበት፡፡

# <u>ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ</u>

***ቅዱስ ቁርባን***

- **ከምስጢራተ ቤ/ክ አንዱና በመንፈሳዊ ሕይወታችን ጥልቅ ተጽእኖ የሚፈጥር ለምንቀበለውም ብዙ መንፈሳዊ ሀብታትን የሚያድል ነው፡፡**
- **ከእግዚአብሔር ጋር ስንኖር የምናገኘው የመጀመሪያው ጥቅም ነው፡፡** ‹‹ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።›› **ዮሐ 6፡56፡፡**
- **ለሰው መንፈሳዊ ሕይወትን የሚያድል የሕይወት ምግብ ነው፡፡** ‹‹የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና አላቸው። የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና አላቸው። ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።›› **ዮሐ 6፡33፡48፡50፡51፡፡**
- ‹‹ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም።›› **ዕብ 9፡22፡፡ እንደተባለ ስለ ኃጢአታችን የቀረበ** ‹‹የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።›› **ቀዳ ዮሐ 1፡7፡፡ ነው፡፡**
- **ዘወትር በቅዳሴ ቤተ ክርስቲያን ‹‹ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ ...›› በማለት ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን የምንገባበት ምስጢር ነው፡፡** ‹‹ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።›› **ቀዳ ቆሮ 11፡26፡፡ እንዳለ፡፡**

# ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

## *ለቅዱስ ቁርባን የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት*

- ቅዱስ ረዊስ ‹‹ቅድስት ድንግል ማርያም መለኮትን ለመሸከም በውስጥም በውጭም ንጹሕ ሆና እንደተገኘች ቅዱስ ቁርባን የሚቀበሉ ሁሉ በውስጣቸው ንጹሐን ሁነው ይዘጋጁ፡፡›› እንዳለ ወደ ቅዱስ ቁርባን ለመቅረብ ዝግጅት ያስፈልገዋል፡፡
- ቅዱስ ቁርባንን መቀበል ብቻ ሳይሆን ለመንፈሳዊ በረከት ለመብቃት የሚያስችሉንን መንገዶች በአትኩሮት መከታተል ያስፈልገናል፡፡ በምሴተ ሐሙስ ቅዱስ ቁርባንን አሥራ አንዱም ቢቀበሉም በመጨረሻ በመስቀሉ ሥር ለተዘጋጀላቸው ሽልማት የበቃው ግን ቅዱስ ዮሐንስ ነበር፡፡ ከእነርሱም አንዱ እስከ ሊቶስጥራ ድረስ በርትቶ ቢደርስም የማልኮስን ጆሮ በመቁረጥ፣ ጌታውን አላውቀውም ብሎ በመካድ ሲገኝ ሌሎቹ ዘጠኙ ግን ተሸሽገዋል፡፡ ይህም የሚያስረዳን ቅዱስ ቁርባንን ብቻ ሳይሆን በረከቱንም ለመቀበል በሚያስችለን መንገድ የመዘጋጀትን አስፈላጊነት ነው፡፡ ዝግጅቶቹም የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ***በትሑት ልቦና መሰናዳት***

- የሚቀድሰው ካህን ከቅዳሴው በፊት የመዘጋጀት ጸሎት ያቀርባል፡፡ እንግዲህ ካህኑ መጸለይ ካስፈለገው ከእጁ ቅዱስ ቁርባንን የሚቀበሉስ ምን ያህል መዘጋጀት ያስፈልጋቸው ይሆን?

# ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

## *ለቅዱስ ቁርባን የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት*

### *2. በንስሐና በንጽሕና መሰናዳት*

- ‹‹ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጐናጸፋል፡፡›› **ራእ 3፡5፡፡ እንዳለ ካህናት በቅዳሴው ሰዓት የሚለብሱት ልብስ መንፈሳዊ ንጽሕናን የሚያመለክት ነው፡፡**
- **ካህኑም በቅዳሴው ሰዓት እጁን መታጠቡ በንስሐ ነፍስን የማንጻትን አስፈላጊነት ለማስታወስ ነው፡፡**
- **ጌታችን** ‹‹እናንተም ንጹሐን ናችሁ፥ ነገር ግን ሁላችሁ አይደላችሁም፡፡›› **ዮሐ 13፡10፡፡ ማለቱ ንጹሕ ሆኖ በንስሐ ጸድቶ ያልቀረበው ይሁዳን እንደለየው ለማመልከትና ከቅዱስ ቁርባን በፊት በንስሐ እንድንጸዳ ሊነግረን ነው፡፡**
- **ዲያቆኑ ተመልከት ማለቱን ተከትሎ ካህኑ ቅድሳት ለቅዱሳን ማለቱም የተቀደሰው የሚገባው በንስሐ ምስጢር ለተቀደሱ ነው ማለቱን ልብ እንበል፡፡** ‹‹እርሱ ሳሙኤልም፡- ለደኅንነት ነው ለእግዚአብሔር እሠዋ ዘንድ መጣሁ ቅዱሳን ሁኑ፥ ከእኔም ጋር ወደ መሥዋዕቱ ኑ አለ። እሴይንና ልጆቹንም ቀደሳቸው፥ ወደ መሥዋዕቱም ጠራቸው።›› **ቀዳ ሳሙ 16፡5፡፡**

# ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

***ለቅዱስ ቁርባን የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት***

## *3. አካላዊ ዝግጅት*

- ሕዝበ እስራኤል አሠርቱ ትእዛዛትን ለመቀበል ልብሳቸውን በማጠብ፣ ከሚስቶቻቸው ጋር ከግኑኝነት በመራቅ… እንዲዘጋጁ እንደተነገራቸው አካላዊ ዝግጅት እናደርጋለን፡፡ ‹‹ሙሴም ከተራራው ወደ ሕዝቡ ወረደ፥ ሕዝቡንም ቀደሰ ልብሳቸውንም አጠቡ። ሕዝቡንም። ለሦስተኛው ቀን ተዘጋጁ፥ ወደ ሴቶቻችሁ አትቅረቡ አለ።›› ዘጸ 19 14-15፡፡
- ቅዱስ ቁርባንን በምንቀበልበት ዕለት ግብረ ሥጋ፣ ጸጉርን መላጨት፣ ጥፍርን መቆረጥ ያስቀራሉና እንደተሠራልን ሥርዓት የምንቀበል ከሆን በሥጋም በነፍስም ዝግጁ እንሁን፡፡
- ከ14-18 ሰዓታት በመጾም መዘጋጀት አለብን፡፡

## *4. በእርቅ መዘጋጀት*

- በቅዳሴ እንደምንጸልየው ሁላችን ከሰሙነ ሕማማት ውጪ በፍጹም ሰላምታ በመሳሳም የምንለዋወጥበት ፍቀር እንዲኖረን ያስፈልጋል እንጂ ማጎንበስ ብቻ አይደለም፡፡
- ከእግዚአብሔር ጋር ስለመታረቅ ‹‹ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።›› ካል ቆሮ 5፡20፡፡ እርስ በርስ ስለመታረቅም በማቴ 5፡23-24 እንደተነገረን የተጣላነውን በመታረቅ ለቅዱስ ቁርባን ዝግጅት እናድርግ፡፡

# ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

## *ለቅዱስ ቁርባን የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት*

### *4. በእርቅ መዘጋጀት*

- **ከበደልን ይቅርታ በመጠየቅ ከተበደልን ልቦናችንን ከጥላቻ በመጠበቅ እንገኝ፡፡**
  - ‹‹በከንቱ የሚጠሉኝ ከራሴ ጠጕር በዙ፡፡›› **መዝ 68(69)፡4፡፡ እንዳለ ሳዖል ዳዊትን ጠልቶት ነበር፤ ጌታችንም ያለ ምክንያት ተጠልቷል፡፡** ‹‹ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ እወቁ። ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር፤ ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል። ባርያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን ቃል አስቡ። እኔን አሳደውኝ እንደ ሆኑ እናንተን ደግሞ ያሳድዱአችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው እንደ ሆኑ ቃላችሁን ደግሞ ይጠብቃሉ። ዳሩ ግን የላከኝን አያውቁምና ይህን ሁሉ ስለ ስሜ ያደርጉባችኋል። እኔ መጥቼ ባልነገርኋቸውስ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን ለኃጢአታቸው ምክንያት የላቸውም። እኔን የሚጠላ አባቴን ደግሞ ይጠላል። ሌላ ሰው ያላደረገውን ሥራ በመካከላቸው ባላደረግሁ፥ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን እኔንም አባቴንም አይተውማል ጠልተውማል። ነገር ግን በሕጋቸው። በከንቱ ጠሉኝ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።›› **ዮሐ 15፡18፡24-25፡፡ እንዳለን ከእነዚህ መታረቅ ባንችልም ከጥላቻ ግን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡**
  - ‹‹**ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል፡፡**›› **ቀዳ ቆሮ 15፡33 እንደተባልን በሞራል፣ በብቃትና በመንፈሳዊነት የሚያበላሹንን ይቅርታ መጠየቅ አይጠበቅብንም፤ መጽሐፍም ወደ ጥፋት ከሚመሩን እንድንጠበቅ ይመክረናልና፡፡**

# ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

## ***ለቅዱስ ቁርባን የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት***

### *4. በእርቅ መዘጋጀት*

- ክህደትንና ሐሰትን ጥርጥርንም ከሚያስፋፉ ጋር መታረቅ አይጠበቅብንም፡፡ ካል ዮሐ 10-11፣ ቀዳ ቆሮ 5፡13፡፡
- እንግዲህ እርቅ ስንል ከሌሎች ጋር ስምምነትን የምንፈጥረው ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረንን ግኑኝነት ለኪሳራ ዳርገን መሆን እንደሌለበት እናስተውል፡፡

### *5. አብዝቶ በመጸለይ መዘጋጀት*

- ‹‹የሚገባኝ ሆኜ ሳይሆን ስላስፈለግኸኝ ለመፍትሔዬ ስል እቀበላለሁ፤ ወደፊት በመንፈሳዊነት ለመራመድ ስል፣ የቅድስናን ሕይወት ለመምራት ስለምፈልግ... እቀበልሃለሁ›› እያልን አብዝተን በመጸለይ እንዘጋጅ፡፡ እንዲህ የሚቀበሉም ኃጢአትን ከመሥራት ነጻ ይወጣሉ፡፡
- ‹‹ ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት። ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና። ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል። ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር፡፡›› ቀዳ ቆሮ 11፡27-31፡፡
- ከተቀበልንም በኋላ በባዶ እግር ከመሄድ፣ ሩቅ መንገድ ከመጓዝ፣ ውሃ ከመታጠብ፣ ከመድማት፣ ራቁታችንን ከመሆን፣ ክፉ ቃላትን ከመወርወር ... እንጠበቅ፡፡ ወደ እኛ በጎ ያልሆነ እንዳይገባና እንዳይወጣ እንጠንቀቅ፡፡

# ንስሐ - ቅዱስ ቊርባንና - ስጦታ

## *መስጠት*

- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው፡፡›› የሐዋ 20፡25፡፡ ጌታችንም ‹‹ብራብ አበላችሁኝ፣ ብጠማ አጠጣችሁኝ፣ እንግዳ ሆኜ ብመጣ ተቀብላችሁ አስተናገዳችሁኝ፣ ብታረዝ አለበሳችሁኝ፣ ብታመም ጠየቃችሁኝ፣ ብታሰር ጎበኛችሁኝ፡፡›› ማቴ 25፡35-40፡፡ ያለን መስጠት ለሌላው ማካፈል መሆኑን እንድንረዳ ነው፡፡
- የገዛ ማንነቱን የረሳ ሰው አይሰጥም አይቀበልም፣ ራስ ወዳድ የሆነም ሰው ይቀበላል አይሰጥም፡፡
- ራስ ወዳድ ያልሆነ ሰው ግን ይሰጣል አይቀበልም፡፡
  - ከራሱ እየወሰደ ለሌላው ይሰጣል፡፡ የሰራፕታዋ መበለት ለነቢዩ ኤልያስ ያደረገችው ይህን ነው፡፡ ቀዳ ነገ 17፡11-19፡፡
  - ያቺ ድሃ መበለትም ከድህነትዋ ብቻ ሳይሆን ያላትን ሁሉ ስለሰጠች ጌታችን ባረካት፡፡ ሉቃ 21፡14፡፡
  - እንዲህ ያሉ ሰዎች ለሌሎች ሰጥቼ እኔ ተርቤ ልሙት እስከማለት ይደርሳሉ፡፡

1. ***እግዚአብሔር የሚመለከተው የምንሰጠውን  ስጦታ ብዛት ሳይሆን ለመስጠት ያለንን ፍላጎት ነው***

- በአግባብ የሚሰጥ ሰው የሚሰጠው ለመስጠት ሲል ብቻ ሳይሆን የሚሰጣቸውን ስለሚወድ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ሰው ሲሰጥም ሳያማርር፣ ሳይገደድ፣ ሳይገፋ ይሰጣል፡፡ እግዚአብሔርም ‹‹እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም።›› ካል ቆሮ 9፡7፡፡
- ሕዝቡ በብሉይ ለቤተ መቅደሱ ሥራ በደስታ ስለሰጡ ተባርከውበታል፡፡ ቀዳ ዜና 29፡9-16፡፡
- ‹‹ሁሉ ካንተ ዘንድ ነውና ከእጅህ የተቀበልነውን መልሰን ሰጥተንሃል፡፡›› ቀዳ ዜና 29፡14፣ ኢዮ 1፡21፡፡

## ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

**_2. ሁሉ ከርሱ ከሆነ ከእኛ መልሶ መቀበሉ ፍጹም ትሕትና እንደሆነ ልብ እንበል_**

- ምድርና መላዋ የእርሱ የሆነች እግዚአብሔር የሰጠንን መልሰን በመስጠት በኩል ስሜታችንን መግለጫ እድል አዘጋጅቶልናል፡፡ መዝ 23(24)፡1፡፡
- አባት ከገዛ ገንዘቡ ሰጥቶ ልጁ ስጦታ ገዝቶ ሲመጣ እንደሚቀበለው ስለወደደን በመስጠት ቤቱን፣ ልጆቹን እንድንከባከብ ፈቀደልን፡፡
- ቀናትን ሰጠንና በሳምንት አንድ ቀን፣ አንድ ቀንም ሰጥቶን 2 ሰዓት ከ24 ደቂቃ ስጡኝ በማለት መስጠትንና በመስጠትም የሚገኘውን በረከት አሰናዳልን፡፡
- ስለዚህ ጤናን ስጠኝና በርሱ ላገልግልህ፡ ጤናና ብርታት ካንተ ዘንድ ነውና፤ እንድወለድ ባታደርገኝ አልኖርም፣ አላገለግልህምም ነበር፤ አሁንም ካንተ የተቀበልሁትን መልሼ እሰጥሃለሁ… እንበለው፡፡

**_እንዴት እንስጥ?_**

**ስንሰጥ በሐሳብም፣ በንግግርም፣ በልብም ክብርን ባለመፈለግ ይሁን ከራሳችን አልሰጠንምና፡፡**

- ‹‹ ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለ ምንድር ነው?›› ቀዳ ቆሮ 4፡7፡፡
- ስጦታችንም በምስጢር እንዲሆን ታዘናል፡፡ ማቴ 6፡1-4፡፡
- ስጦታችንን መሰወር ያለብን ከሰው ብቻ ሳይሆን ከራሳችንም ጭምር ነው፡፡
- ስንት እንደሰጣችሁ አትቁጠሩ፣ ወደ ኋላ ተመልሳችሁም አታስታውሱት፣ የሰጠችሁትንም ሁሉ አትናገሩ ይልቁኑ እርሱት እንጂ፡፡… ስንተ እንደሰጠን እርሱ ያውቃልና፡፡
- ሰይጣን ዋጋችሁን በምድር እንድትቀበሉ ይዋጋችኋልና ራሻችሁን በማክበር ከመስጠት ተቆጠቡ፡፡

# ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

## ያለ አድልዎ በልግስና መስጠት

- ‹‹የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፡፡›› እንዳለ  ሮሜ 12፡8፣ ቀዳ ጢሞ 6፡18፣ ካል ቆሮ 9፡6፡፡
- ንጉሥ ዳዊት የኢያቡሳዊውን የኦርናን አውድማ ለመግዛት ሲነሳ ኦርና በነጻ ሊሰጥ ተስማማ፤ ንጉሥ ዳዊት ግን ገዛ፡፡ ሁለቱም በልስና ያለጉድለት ለመስጠት ተስማምተዋል፡፡ ካል ሳሙ 24፡22፡፡
- ሥላሴ ድንኳኑን ሲጎበኙ አብርሃምም ያደረገው ይህንኑ ነው፡፡ ዘፍጥ 18፡6-8፡፡ እንግዶቹ ወተት፣ ቅቤ፣ ሥጋ የሚፈልጉ ሁነው ባይገኙም ለአብርሃም ግን በልግስና ከልብ መስጠት ደስታው ነበር፡፡
- ጌታችንም ‹‹ስጡ ይሰጣችሁማል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፥ የተጨቈነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል።›› ሉቃ 6፡38፣ ‹‹ያለህን ሽጠህ ለድሆችና ለጦም አዳሪዎች ስጥ፡፡›› ማቴ 19፡21፣ ሉቃ 3፡11፡፡

## ሳንጠየቅ መስጠት

- የሰማዩ አባታችን ለእኛ፣ ወላጆችም ለልጆቻቸው የሚያደርጉት ይህንኑ ነው፡፡ለቤ/ክንም ሆነ ለሰዎች ሳንጠየቅ የሚፈለገውን እናድርግ፡፡
- ስንሰጥም አንዘግይ፡ መዘግየት ስጦታው የሚያስፈልጋቸውን ይጎዳልና፡፡ ‹‹ለተቸገረው ሰው በጎ ነገርን ማድረግ አትከልክል፥ ልታደርግለት የሚቻልህ ሲሆን። ወዳጅህን ሂድና ተመለስ ነገ እሰጥሃለሁ አትበለው። በጎ ነገርን ማድረግ ሲቻልህ።›› ምሳ 3፡27-28፡፡
- ስንሰጥም የማንፈልገውን ያረጀውን ሳይሆን አዲሱንም መልካሙንም እንስጥ፡፡ የምንሰጠው ለክርስቶስና ለድሆች ነውና፡፡ ታዲያ በስጦታችን የምንመስለው አቤልን ወይስ ቃየንን? እኛስ እንደ አቤል የበለጠውን እናቅርብ፡፡

# ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

- በዘመነ ሐዋርያት ሰዎች ያላቸውን ሁሉ ሸጠው ይሰጡ ነበር፡፡ የሐዋ 4፡34-35፡፡ ታዲያ የእኛ ስጦታስ ወዴት አለ?
- አቤል ከአባቱ አዳም እንደተማረው መልካሙን መሥዋዕት አቀረበ፣ በመቀጠልም ኖኅ ዘፍጥ 8፣ አብርሃም ዘፍጥ 12፣ ኢዮብ 1፡5፣ ሙሴ በዘሌዋ እና በዘጸ 12፣ ዛሬም ብዙዎች ከብሉይ በተለየ የተወደደ መልክ ስጦታቸውን ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ፡፡ ስጦታዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡-

አሥራት

- ያዕ ዘፍጥ 28፡20-22 እንደተጻፈው ስለ አሥራት ለመልከጸዴቅ ካቀረበው ከአባቱ ከአብርሃም ተምሯል፡፡ ዘፍጥ 14፡20፡፡
- አሥራት በዘመነ ሙሴ ሕግ ሆኖ ተሰጥቶናል፡፡ ዘዳግ 14፡22፣ ዘሌዋ 27፡30፣ ዘዳግ 12፡17፣ ዘዳግ 14፡23፣ ዘሌዋ 27፡32፣ ሉቃ 18፡12፡፡
- ከሕዝቡም የተቀበሉትን አሥራትም ካህኑ ለእግዚአብሔር የአሥራት አሥራት አድርጎ ያቀርበው ነበር፡ ዘኁል 18፡26-28፡፡
- አሥራትን የማይከፍል እንደሌባ ይቆጠራል፡፡ ሚል 3፡8-10፡፡
- አሥራትን አለመክፈል ለቤ/ክንና ለድሆች ኢፍትሐዊ መሆን ነው፤ የገንዘቡ ትክክለኛ ባለቤቶች እነርሱ ናቸውና፡፡ ሉቃ 16፡9፡፡ እነዚህም ቤ/ክንና ድሆች ስለእኛ የሚጸልዩ ናቸው፡፡
- ምንም ያህል አስፈላጊና አስገዳጅ ነገር ቢገጥመን አሥራትን በመክፈል ድሃ አደጎችን፣ ባልዋ የሞተባትን፣ … እንድረስላቸው፡፡ አዎ የሚያስፈልጋቸውን እንስጣቸው፡፡ ቀዳ ጢሞ 5፡8፡፡

# ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

## አሥራት

- አሥራት ስንከፍልም ከቋሚ፣ ከተንቀሳቃሽ ንብረጻችን የእግዚአብሔርን ቀንሰን በእግዚአብሔር ሳጥን እናስቀምጥ።
- ሁሉንም ነገር ለራሳቸው ከተጠቀሙ በኋላ የተረፈ ካለ እግዚአብሔርን የሚያስቡትን አንምሰላቸው፤ እኛስ ቀድመን የእርሱን እናስቀምጥ... እነርሱ እግዚአብሔርን መጨረሻ ያደርጉታል ፈጽመውም ይረሱታልና እንደሌሎቹ የገቢያችን ተቀናናሾች ቀድመን የእግዚአብሔርን ቀንሰን እንስጥ።
- አሥራት ከምንሰጣቸው ስጦታዎች ትንሹ ነው። በአዲስ ‹‹ለሚጠይቃችሁ ስጡ።›› ማቴ 5፡42፣ ‹‹ለራሳችሁ በምድር መዝገብ አታከማቹ።›› ማቴ 6፡19-20 ስለዚህ አሥራትን በመስጠት ብቻ አንርካ
- አሥራት ስንከፍልም የእግዚአብሔርን እዳ ከፈልኩ አንበል። ‹‹የድሀውን ጩኸት እንዳይሰማ ጆሮውን የሚደፍን ሰው፥ እርሱ ራሱ ይጮኻል አይሰማለትምም።›› ምሳ 21፡13።
- ከእግዚአብሔር፣፣ ከቤ/ክ፣ ከድሆች ጋር ልቦና ኅድሎን በስሌት ብቻ ለመግባባት አንጣጣር። ስንሰጥም ከቀራጮች የተሻልን ሆነን እንስጥ። ‹‹ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ ወደ መንግሥተ ሰማያት አትገቡም።›› ማቴ 5፡20 ተብለናልና። እነርሱ ሥራት ይከፍላሉ ነገር ግን በፍቅርና ከልብ አልነበረም።
- አሥራት ክፈሉ ስንባል ‹‹ያለህን ሸጠህ ለድሆችና ለጦም አዳሪዎች ስጥ።›› ማቴ 19፡21 ሲባል እየከፋው እንደተመለሰው ሰው ሆነን እንዳንገኝ እንጠንቀቅ።
- አሥራት እግዚአብሔር ለእኛ ከሰጠው ስጦታ ብቸኛ ድርሻው አይደለም።

## ንስሐ - ቅዱስ ቁርባንና - ስጦታ

**በኩራትና ቀዳምያት**

- ከእንስሳም፣ ከተክልም፣ ከፍራፍሬም፣ ከዛፍም፣ ከምርት ሀሉ የመጀመሪያው ለእግዚአብሔር ነው፡፡ ዘጸ 13፡2፣ ዘጸ 23፡19፣ ሕዝ 44፡30፣ ዘሌዋ 23፡10፣ ዘጸ 13፡12-13፣ ዘጸ 34፡19፡፡
- ስለ ጌታችንም በ40ኛው ቀን ስጦታ ይዘው ወደ ቤተ መቅደስ እንደቀረቡ ተጽፎልናል፡፡ ሉቃ 2፡22-23
- ከልጆችም መካከል ልጅንም ለእግዚአብሔር መስጠት ይገባል፡፡
- በኩራት መስጠት አሥራት ከመክፈል ይከብዳል፡፡ ነገር ግን ሐና ሳሙኤልን፣ ኤልሳቤጥ ዮሐንስን ለጌታ ለመስጠት አልሳሱም፡፡
- እግዚአብሔር ከሁሉም መጀመሪያውን የሚወስድ ነው፡፡
- ዛሬ ሁላችንም ገበሬዎች ስላልሆንን የመጀመሪያውን ወር ደመወዝ፣ ወይም የመጀመሪያውን ገቢ… እንስጥ፡፡ የመጀመሪያውን ደመወዝ ጭማሪ፣ ለዶክተሮች የመጀመሪያውን ታካሚ ገቢ፣ ለመምህራን የመጀመሪያውን ተማሪ ገቢ… መስጠት ይገባል፡፡

**ስዕለት**

- መክብብ 5፡2-6፡፡
- ለመሳል አንቸኩል ከተሳልን ደግሞ ስዕለታችንን እንፈጽም፡፡

**መባዕ**

- ቤ/ክ መባዕ (ዕጣን፣ ጧፍ፣ ዘቢብ፣ መገበሪያ፣ መጻሕፍቱን፣ ነዋየ ቅድሳቱን፣ … ስለሚሰጡ ትጸልያለች፡፡ የምትፈልገው መብራት ቢሆን አቅርበን በጸሎቱ ለመጠቀም እንብቃ፡፡
- ‹‹በፊቴ ባዶ እጅህን አትታይ፡፡›› ዘጸ 23፡15፣ ዘጸ 34፡20 እንደተጻፈልን፡፡ ያስፈጽመን፡፡ አሜን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org